በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር---239455
ቀን- ጥቅምት 05 ቀን 2016 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

ረታ ቶሎሳ

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ኑረዲን ከድር

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት - የቀረበ የለም

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ አዲሴ ተፈራ - አልቀረቡም

2. ሃዋዩ የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ማይክሮ ኢንተርፕራይዝ ማሕበር - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ከዉል ዉጭ ኃላፊነት የሚመለከት ሲሆን የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ ሲሆኑ የአሁን አመልካች ተከሳሽ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ ነበሩ፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 48018 ጥቅምት 08 ቀን 2015 ዓ.ም ተሰጥቶ እና በኦሮሚያ ክልል

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 390450 ታሕሳስ 12 ቀን 2015 ዓ.ም ተሻሽሎ የተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ።

1ኛ ተጠሪ የካቲት 21 ቀን 2014 ዓ/ም በተጻፈ ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- የአሁን አመልካች ፍልጥ ለመሆን የደረሰ ባህርዛፍ ቁጥሩ 1,800፤ ግምቱ 1800 x 40 x 15 = ብር 1,080,000/አንድ ሚሊየን ሰማኒያ ሺ/ ብር የሚሆነዉን በ2012 ዓ/ም የአሁን 1ኛ ተጠሪ የኤሌክትሪክ መስመር ለመዘርጋት ቆርጦ ከጥቅም ዉጪ ያደረገባቸዉ በመሆኑ ለ15 ዓመት ማግኘት የሚገባቸዉንና የቀረባቸዉን ገቢ ስላሳጣቸዉ ለባህር ዛፉ እንክብካቤ ያወጡትን ጨምሮ በጥቅሉ ብር 1,120,000/አንድ ሚሊየን አንድ መቶ ሃያ ሺ ብር/ እንዲሁም የጠበቃ አበል፤ የዳኝነት ክፍያ እና ያወጡትን ሌሎች ወጪዎችን እንዲከፈላቸው እንዲወሰን ጠይቀዋል።

የአሁን አመልካችም በስር ፍ/ቤት ባቀረበዉ የጽሁፍ ምላሽ፡- የእንጨት ምሶሶ የኤሌክትሪክ ፖል የቆመዉ በ1989 ዓ/ም ሲሆን ምንም ተቃዉሞ ሳይነሳ በ2008 ዓ/ም በማደስ የኮንክሪት ፖል ያቆሙ በመሆኑ የካሳ ጥያቄዉ በይርጋ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል። የተጠየቀዉን የካሳ ግምትም የሚቃወሙት መሆኑን፤ የሚጠየቅ ቢሆን እንኳን መክፈል ያለበት የአንድ ዓመት የታጣ ገቢ ግምት ብቻ ነዉ። እንዲሁም የኤልክትሪክ ፖሉን በ2007 ዓ/ም በኮንትራክተርነት በመስማማት አቁሞ በ2014 ዓ/ም ያስረክበበዉ የአሁን 2ኛ ተጠሪ ስለሆነ ካሳ መክፈል የሚገባዉ አመልካች ባለመሆኑ 2ኛ ተጠሪ ወደ ክስ እንዲገባ እንዲደረግ በመጠየቅ ተከራክሯል።

የአሁን 2ኛ ተጠሪም በተከሳሽነት ወደ ክርክሩ በመግባት በተሰጠዉ ዲዛይን መሰረት ግንባታ የፈጸመ መሆኑን በመግለጽ ተጠያቂነት የሌለበት መሆኑን በመግለጽ ክርክሩን አቅርቧል።

የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ እና ጉዳዩን ካጣራ በኋላ መዝገቡን መርምሮ፡- 2ኛ ተጠሪ ተጠያቂነት የለበትም፤ የአሁን አመልካች ለፍልጥነት የደረሱ የ1ኛ ተጠሪን ባህርዛፍ መጠቀም እንዳይችል የኮንክሪት ፖል በማቆም ጉዳት ማድረሱ፤ የጠፋዉ ባህርዛፍ በሶስት ዓመት አንድ ጊዜ እንደሚደርስ፤ በ15 ዓመት ዉስጥ ደግሞ ለፍልጥ የደረሰ ባህርዛፍ 1ኛ ተጠሪ ለ5 ጊዜ ቆርጠዉ ሊጠቀሙ እንደሚችሉ በማስረጃ ተረጋግጧል። በመሆኑም በድምሩ የአሁን አመልካች የእንክብካቤ ወጪን ጨምሮ 113,800 ብር ከወጪ ኪሳራ ጋር እንዲሁም ከጠበቃ አበል ጋር ለ1ኛ ተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል። በተሰጠዉ ዉሳኔ ላይም የአሁን አመልካች ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታዉን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ምዕራብ ምድብ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ መዝገቡን በመመርመር በስር ፍ/ቤት ከተሰጠዉ ዉሳኔ የእንክብካቤን ወጪ ብር 40,000/ዓርባ ሺ ብር/ በመቀነስ የ1ኛ ተጠሪ ለፍልጥ የደረሰ 246 የባህርዛፍ እንጨት የአሁን አመልካች ለመብራት ፖል ዝርጋት ስለቆረጠ በ15 ዓመት ዉስጥ በየ3 ዓመቱ ሊያስገኝ የሚችል የአሁን 1ኛ ተጠሪ የተከለችዉ የ1 ባህርዛፍ ዋጋ በ60 ብር ተሰልቶ የሚመጣዉ አጠቃላይ ብር 73,800/ሰባ ሦሥት ሺ ስምንት መቶ ብር/ እንዲከፍል፤ በተወሰነዉ ገንዘብ በታሪፍ የዳኝነት እንዲከፍሉ እንዲሁም የጠበቃ አበል በተወሰነዉ ገንዘብ መጠን በ15% ተሰልቶ ይክፈል በማለት የስር ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታዉም ሊቀርብ የቻለዉ ይህ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- ከአራት ዓመት በፊት የኤልክተሪክ መስመር ዝርጋታ ሥራ ካለምንም ተቃዉሞ ሰርተን አጠናቀን ባለንበት ሁኔታ 1ኛ ተጠሪ በ2012 ዓ/ም ባህርዛፍ ቆርጠዉብኛል በማለት ላቀረበዉ ክስ ያቀረብነዉን የመ/ደ/መቃወሚያ የስር ፍ/ቤት ዉድቅ በማድረግ ወደ ፍሬ ነገር መግባቱ፤ የተጠየቀዉን የካሳ አሰላልን በተመለከተም ባህር ዛፍን እንደ ሌላ ተክል በየዓመቱ ፍሬ እንደሚሰጥ በመቁጠር የሦስት ዓመት ግምት በአምስት ተባዝቶ እንድንከፍል መወሰኑ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 45401 ላይ የሰጠዉን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚጻረር በመሆኑ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪም የኤሌክትሪክ ዝርጋታዉን ለማከናወን ዲዛይኑን በራሱ አዘጋጅቶ በኮንትራት ወስዶ ስራዉን አጠናቅቆ ባላስረከበን ሁኔታ፤ የእኛን ፈቃድ ሳይጠይቅ ላደረሰዉ ጥፋት ተጠያቂ መሆን ሲገባዉ የስር ፍ/ቤት አመልካችን ተጠያቂ በማድረግ 2ኛ ተጠሪ በነጻ እንዲሰናበት ዉሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ዉሳኔዉ ሊሻር ይገባል የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለተጠሪ የተወሰነዉ የባህርዛፍ ግምት ካሳ እንደ ሌሎች የሰብል ግምት ታስቦ በ5 ዓመት ተባዝቶ የተወሰነበት አግባብ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መ/ቁ. 45401 ከሰጠዉ ትርጉም አንጻር” ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጎ በጽሁፍ ክርክር ተደርጓል፡፡

1ኛ ተጠሪን በሚመለከት ጥሪ ተደርጎላቸዉ መልስ ሊያቀርቡ ባለመቻላቸዉ ፍ/ቤቱ በጽሁፍ መልስ የማቅረብ መብታቸዉን አልፎታል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

2ኛ ተጠሪ ያቀረበዉን መልስ ይዘት በአጭሩ ስንመለከትም፡- ከአመልካች ጋር ባደረጉት ስምምነት በሙያቸዉ የኤሌክትሪክ ዝርጋት ሰርተዉ ለማስረከብ ዉል ፈጸሙ እንጂ በ3ኛ ወገን ንብረት ላይ የሚደርስ የንብረት ጉዳት ምንም ዓይነት ኃላፊነትም ሆነ የዉል ፍጹታ አልገቡም፡፡ ጉዳት ደርሷል በተባለዉ ጊዜ በ2012 ዓ/ም በአካባቢዉ በነበረዉ የፀጥታ ችግር ምክኒያት ሥራ ያቆሙ በመሆኑ እና ጉዳት ደርሷል ተብሎ ክስ የቀረበበትንም ቦታ በ2010 ዓ/ም ሥራዉን ሠርተዉ አጠናቅቀዋል፡፡ በቦታዉ ተገኝተዉ በሥራ ላይ ሳይኖሩ በዚህ ጉዳይ ለጠፋ ንብረት ልንጠየቁ አይገባም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ምንም አይነት መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ዉድቅ ተደርጎ ዉሳኔዉ እንዲፀና በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ ጭብጥ ለተጠሪ የተወሰነዉ የባህርዛፍ ግምት ካሳ እንደ ሌሎች የሰብል ግምት ታስቦ በ5 ዓመት ተባዝቶ የተወሰነበት አግባብ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መ/ቁ. 45401 ከሰጠዉ ትርጉም አንጻር ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

ጉዳት መድረሱ ምክንያታዊ በሆነ እርግጠኝነት ሲረጋገጥ በመርህ ደረጃ በተቻለ መጠን የጉዳት ካሳው መጠን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2090 እና 2091 መሠረት ከደረሰው ወይም ወደፊት ሊደርስ ከሚችለው ጉዳት ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን ተገቢውን ጥንቃቄ ተደርጎ ሊወሰን የሚገባዉ ነዉ፡፡ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትንና ለንብረት ካሳ የሚከፈልበትን እና ተነሺዎች መልሰዉ የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 1161/2011 አንቀጽ 13(1) በቋሚነት ስለሚነሳ የገጠር መሬት ባለይዞታ የሚሰጥ ካሳ ምትክ ቦታ የተሰጠዉ ከሆነ የአንድ ዓመት ገቢዉ በወቅታዊ ዋጋ ተሰልቶ የልማት ተነሽ ካሳ የሚከፈለዉ ሲሆን ትክ ቦታ ያልተሰጠዉ ከሆነ ግን የዓመታዊ ገቢዉ በ15 ዓመት ተባዝቶ የልማት ተነሽ ካሳ መከፈል ያለበት መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ ለዘለቄታዉ የተፈናቀለና ትክ መሬታ ያልተሰጠዉ የገጠር መሬት ባለይዞታ የሰብሉ ወይም ተክሉ ዓይነት ግምት ዉስጥ ሳይገባ የሚከፈለዉ ካሳ በ15 ዓመቱ የሚያገኘዉ ገቢ ሆኖ የሚሰላዉ ግን ዓመታዊ ገቢዉ ከታወቀ በኃላ በ15 ዓመት ተባዝቶ መሆኑን ነዉ፡፡ የገቢዉ ምንጭ ባሕርዛፍ ሲሆን ይህ ሊሰላ የሚችለዉ በ15 ዓመት ጊዜ ዉስጥ ባሕርዛፍ ምን ያህል ጊዜ ምርት ይሰጣል የሚለዉ ከታወቀ በኃላ የአንድ ጊዜ ምርት በሚያስገኘዉ ገቢ በማባዛት ሊሆን ይገባል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በሌላ በኩል ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 45401 ባሕርዛፍ በመቁረጥ የደረሰዉ ጉዳት ግምት ከሚከፈል በቀር በ10 ዓመት ተባዝቶ ሊከፈል አይገባም በማለት የሰጠዉን ትርጉም በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 1161/2011 ከመዉጣቱ በፊት ሥራ ላይ የነበረዉን አዋጅ ቁጥር 455/1997 መሠረት ተደርጎ የተሰጠ ትርጉም ከመሆኑም በላይ ባለይዞታዉ የደረሰበት ጉዳት የአንድ ዘመን ምርት ነዉ ወይስ በዘላቂነት ያጣዉ ነዉ የሚለዉ እንዲሁም ምትክ መሬት የተሰጠዉ መሆን አለመሆኑን በግልጽ የማያስቀምጥ በመሆኑ አዋጅ ቁጥር 1161/2011 መሠረት ተደርጎ ለሚሰላዉ የመፈናቂያ ካሳ ስለት ትርጉሙ አግባብነት የለዉም፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ በ2012 ዓ.ም በኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ መነሻነት ለፍልጥ የሚሆን 246 ባሕርዛፍ ተቆርጦ የወደመባቸዉ መሆኑንና መስመሩ በቋሚነት የሚቀጥል በመሆኑ በቋሚነት ገቢ ማጣታቸዉ እና ምትክ መሬት ያልተሰጣቸዉ መሆኑ ፍሬ ነገርን በማስረጃ አጣርተዉ ለማረጋገጥ ስልጣን በተሰጣቸዉ የስር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ የስር ፍ/ቤት በአንድ ዙር የወደመዉ ባሕርዛፍ 246 ሆኖ የአንዱ ዋጋ ብር 60 መሆኑንና በአንድ ዙር የሚገኘው ገቢ 14,760 እንደሆነ እንዲሁም ምርት የሚሰጠዉ በየሦስት ዓመቱ መሆኑ በባለሙያ መረጋገጡን ተከትሎ በ15 ዓመት ጊዜ ዉስጥ 5 ዙር ምርት እንደሚሰጥ በመዉሰድ በአንድ ዙር የሚገኘዉን ገቢ በአምስት አባዝቶ ብር 73,800 ለ1ኛ ተጠሪ እንዲከፈላቸዉ መወሰኑ የአዋጅ ቁጥር 1161/2011 አንቀጽ 13 ድንጋጌን መሠረት ያደረገ በመሆኑ የሚነቀፍ አይደለም፡፡

የ2ኛ ተጠሪ ኃላፊነትን በተመለከተ በተሰጠዉ ዲዛይን መሠረት የመስመር ዝርጋታዉን አከናወነ እንጂ ከዲዛይን ወጥቶ የፈጸመዉ ጥፋት መኖሩ ባልተረጋገጠበት 2ኛ ተጠሪ ኃላፊነቱን የሚወስድበት ወይም የሚጋራበት አግባብ የለም፡፡

ሲጠቃለል የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በማሻሻል የሰጠዉ ዉሳኔ የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት ባለመኖሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 390450 ታሕሳስ 12 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 18018 ጥቅምት 08 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠዉን ዉሳኔ በማሻሻል የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

2. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ